

# መከራ የለመደ

ያደግሁበት ፍርሀት እስር ግርፋቱ፣
በእድሜ ልኬ ያለው ረሀብ እርዛቱ።
የእናቴ ጣር ጩኸት የአባቴ ሰቆቃ፣
ሰደት መንከራተት በጣይ በጨረቃ።
ሀዘን ተሸካሚው ደንድኖ ጫንቃዬ፣
ጆሮዬም ተላምዶ እሪታና እየዬ ፤
የሱስ ያህል ሆኖ መከራን ለምጄ፣
ሲያሳንሱኝ እሺ ሲረግጡኝም በጄ።

ከስራ አባረሩኝ ሰደዱኝ ልመና፣
ከሚስቴ ነጠሉኝ በዘር ከፈሉና።
መማር ከፉ ብለው ዶክተር አባረሩ፣
ጤና ይጥፋ ብለው ሀኪሙን አሰሩ።
ካገር ይብስ መንደር መሆኑን ሳያውቁ፣
ሀገር ሀገር ያሉ ተማሪዎች አለቁ።
መከራን መሸከም ልማዴ ሆኖብኝ፣
ጉንጭ አቀብላለሁ ጥፊው ሳይታከተኝ።

ሊነጋ ነው ብዬ የልቤን ሳወራ፣
አደባባይ ወጣሁ ከወገንኩት ጋራ።
ሳይነጋ ጨልሞ የሰይጣን መንገዱ፣
የልብ አድራሾቼ ዘብ ጥያ ወረዱ፤
ለምን ብለው ያሉም በጅምላ ታረዱ።
ሀዘን ተሸካሚው ደንድኖ ጫንቃዬ፣
ጆሮዬም ተላምዶ እሪታና እየዬ፤
ፍትህ እጠብቃለሁ እስኪመጣ ብዬ።

አረ ግፉ በቃ ይቁም ይሄ ስቃይ፣
መጠን ያለፈ ነው ለምድሩም ለሰማይ።
በታከተው መኖር ሰግዶ ተለማምጦ፣
ምድር ሳትቀወጥ ትዕግስት ተሟጦ፤
አውቃለሁ የምትል ጠቢብ ነኝ ደብተራ፣
ታጋይ ነኝ የምትል ላገር የምሰራ፣
አቅም አለኝ ባዩ መሸከም አደራ፤
አከርካሪ እሚሰብር የግፍ ጓዝ ጭነሀል፣
ዝምታው ያልቅና ማጣፊያውም ያጥራል።
እወቅበት ትዕግስት ምልጃና ልመና፣
መከራ የለመደ ሞት አይፈራምና።

ከ ትንሳዔ ሚያዝያ 2007